ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

Tel 202291 4217 mailling address: P.O.Box 73337, Washington Dc 20011

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በመጋቢት 25, 2009 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# ፈውስ የምትፈልግ አገር

ኢትዮጵያ ሀገራችን ፤ ፈውስ ገና ያልተገኘላት ሀገር በመሆኗ ፤ አሁንም ፤ በበሽተኛ አልጋ ተቆራኝታለች ። የባዕዳን ምፅዕዋተኛ፤ የጎረቤቶቿ መዘባበቻ ፤ የአምባገነኖች መጫዎቻ ሆና፤ ፍዳ- መከራዋን ታያለች ። በቅርብ ታሪኳ፤ ሦስት ፅነፈኛ ሥርዓቶች ቢፈራረቁባትም፤ ከመሠረታዊ ችግሮቿ ልትላቀቅ አልቻለችም ። የእነኝህ ተፈራራቂ ሥርዓቶት አስተናጋጆች፤ እንደ ፌንጣ ከአንድ ፅንፍ ወደ ሌላኛው ፅንፍ ከመዝለል በስተቀር፤ የሀገሪቱን መሠረታዊ ችግሮች ፤ ሊፈቱ አልተቻላቸውም ። የእኔ ይሻላል እያሉ የሚያመጡት የአገዛዝ ሥርዓት አራማጆች ሁሉ፤ ከቤተ- ሙከራ ያለፈ ዕርባና አልሰገኘም። የችግሩን ምክንያት ካለመረዳታቸው የተነሳ፤ ፈውሱን እኛው አግኝተነዋል ብለው ሀገሪቱን ከአንድ ማጥ ወደሌላው ማጥ ከመክተት በስተቀር፤ የሚያመጡት ፋይዳ አልነበረም ። የለም ።

የሀገርንና የሕዝብን መሠረታዊ ችግሮች፤ ልክ እንደ ሳይንስ መስተማሪያ ፤ የቤተ -ሙከራ ልምምድ ( ኤክስፐርመንት ) በማድረግ ፤ ሀገራችንን የልጆች መጫዎቻ አደረጓት። የተለያዩ መፍክሮችን እያስነበቡ ፤ በፖለቲካው መድርክ ደነከሩበት። በዳንኪራቸው ያለተሰለፈላቸውን ሕዝብ ፤ ፈጁት። አንደኛው በወታደራዊ አምባገነንነት ሌላኛው በዘር ክፍፍል በሠላም አብሮ የኖረውን ዜጋ ጨፈጨፉት። " ጠብ ያለኽ ዳቦ " እያሉ ያብሮነት ታሪኩን አናጉበት። በመጨረሻም የሚይዙት የሚጨብጡት ሲያጡ ፤ ሀገርን ጎድተው እነርሱም ይወድማሉ ። የአለፉት ስድሳ ዓመታት የሀገራችን ታሪክ ያስመዘገቡት ሠነድ ይመሰክራል ።

ህመሟ ፤ የሰራ-አካላቷን ከላይ እስከታች ስለወረረው ፤ የትኛው መዳህኒት፤ የትኛውን ህመም ሊፈውስ እንደሚችል መርምሮ ያወቀላት ሀኪም ገና እስካሁን አላገኘችም ። በየቀኑ አዳዲስ ድርጅት መፍጠር ብቻውን የሀገሪቱን ችግር የሚፈታ ይመስል ፤ የተያዘ-የተረዘዘው ሁሉ፤ " የራሴን ድርጅት ፈጥሬ እስቲ እኔም ዕድሌን ልሞክረው " በሚል ዕሳቤ ፤ የየራሱን ፍላጎት ማርኪያ የሚሆነውን / የሚፈልገውን ሁሉ ያደርጋል ። ከሱቅ በደረቴ እስከ ሰፈር ኪዎስክ ደረስ የተካተቱ ደርጅቶች እንደ አሸን ከታብ ተፈልፍለዋል ። ሁሉም፤ የየራሱን ስም አስጠሪ ደርጅት መፍጠር ዛሬ በሀገራችን አዲስ ፈሊጥ እየሆነ መጥቷል ። ወይኔ ደግሞ ይኸንን ሂደት አጥብቆ ይፈልገዋል ። ምክንያቱም፤ እንደ ሀረግ-ሬሳ ልፍስፍስ የሆኑ ፤ በራሳቸው ሊቆሙ የማይችሉ ፤ አቅመ-ቢስና ደካማ ድርጅቶች መብዛት ፤ ሊያሰጉት አይችሉምና !

እንዲያውም  ወያኔን ካለማስጋታቸውም  በቀር፤ ብዙዎቹ ፤ የሥርዓቱ ተስፈኞችና ተቅበዝባዦች ሆነዋል ።  ዘረኞቹ ባዘጋጁላቸው ድባብ ወስጥ ገብተው ፤ የነርሱ ፕሮፓጋንዳ ፍጆታ አቀንቃኞች ስለሚሆኑላቸውም ጭምር ነው ።

ዛሬ የሚሊዮን ቁጥር  ትርጉሙ፣ ቅጥ-አምባሩ በጠፋባት ወቅት፤  ሀገርችን ፤ ለመቶ ሚሊዮን  ሕዝብ በባርካታ ሚሊዮኖች የሚቁጠሩ ፖለቲካ ድርጅቶች መፈልፈል ፤ ለሀገርችን ችግሮች  ምን ያኅል መፍተሄ  እንደሚያመጡ፤ ገና በምርምር የተደረሰበት መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ አልተከሰተለትም ።

የቢሊዮን ቁጥር ከተነሳ፤  ወያኔ አዲስ አበባ ከገባ ጀምሮ፤ ለአለፉት 26 ዓመታት  ሀገራችን ሠላሣ/30/ ቢሊዮን ዶላር የውጭ ርዳታ ማግኘቷ  ተመዝግቧል ። በግልባጩ ደግሞ፤ ሠላሣ/30 ቢሊዮን ዶላር ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ  እንደወጣ በመስረጃ ተረጋግጦ ይፋ ሆኗል። ይኸ ወደ ውጭ የኮበለለው ሠላሣ ቢሊዮን ዶላር ፤ የት እንደገባ፤ ምን  እንደዋጠው የሚታወቅ ነገር የለም ።  ታዲያ፤ የወያኔዎቹ ሂሳብ ሲወራረድ ፦

ሠላሣ ቢሊዮን ዶላር  ፦  $ 30 00000000  -  ሲቀንስ ፤ በ$ 30 00000000 =  ውጤቱ  $ 0 / ባዶ ሆኖ ቀርቷል ።

ታዲያ፤ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ  የተዘረፈ ገንዘቡን ለማስመልስ፤

እናንት፦ የጀኒቫ - የዙሪክ ባንኮች፤  ዶላሬን መልሱ  የኋላ  የኋላ  እንዳትከሰሱ!

እያለ ጨኸቱን አስመዝግቦ ተቀምጧል ። የፍርድ ቀኑን ይጠብቃል  ። ፍትኅ-ርትዕ  ይጠይቃል  !  የኢትዮጵያ ሕዝብ የተዘረፈውን ሀብቱን / ዶላሩን  ለማስመልስ  የበረከት ሃብተሥላሴንና የመስፍን ወልደ ማርያምን መርማሪ ኮሚሽን ( ኮሞሲዮን ) መቋቋም አያስፈልገውም ። በወያኔ የተዘረፈው  ብሄራዊ ሃብት ፤ ልክ ለባዕድ  ተቆርሶ እንደሄደው የሀገራችን መሬት ተለይቶ አይታይም ። ሲቻል በህግ ፤ ያለዚያ በሆነው መንገድ መመለሱ አይቀርም ። እኛ " የኋላ ልጅ፤ / ተተኪው ትውልድ ይጨነቅበት ! " አንልም። ችግርንና የዘረ- ድምርን ፤ለተተኪው ትውልድ ማወረስ በታሪክ ያስጠይቃል ። በመጭው ትውልድ ዘንድም ያስወቅሳል ። በዚህ ጉዳይ ላይ ሁሉም ዜጋ በአንክሮ እንዲያስብበት እናሳስባለን !

በርካታ ሚሊዮነሮችና ቢሊየነሮች ሰለተፈጠሩ ፤ በዚያው ልክና ቁጥር የተበራከቱ ድርጅቶች  መኖር አስፈለጊ መሆኑን፤ የኢትዮያ ሕዝብ የሚያምን አይመስለንም ።  ዕምነቱ፤  ፍላጎቱና ጉጉቱ ግን ፤ ድርጅቶች ተጥናክረውና ተባብረው ከዘረኞች አገዛዝ ቀምበር  እንዲያላቅቁት ብቻ ነው ።  የጠንካራ ድርጅቶች መተባበር  ፤ አስፈለጊነት ደግሞ የወያኔን ዕድሜ እነደሚያሳጠረው  ሁሉም ያምንበታል ።  ከኅልፈተ ወያኔ በኋላ ፤ የኢትዮጵያ ችግር በሂደት እየተቀረፈተ እንደሚሄድ፤ ኢትዮጵያ መዳን አለባት ብሎ የሚያምነው ዜጋ ጉጉት ነው።  ከዚያ በፊት ግን ገመምተኛው ሀገራችን፤ ሙሉ ጤናዋን ማግኘት አለባት ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ፤  የውጭ ወራሪ ኃይሎችን ለመከላከል፦

ጎራዴው ሰው በላ ፤ ጦሩ ሰው በላ !  ( ሳንጃ  ለመ ኛታ) እያለ ይዋጋ ነበር።  ዛሬ ደግሞ ፤

ቆሻሻው ሰው በላ ፤ ቆሻሻው ሰው ፈጀ ፤ ናዳው ሕዝብ ዋጠ እያለ ፤ አዲስ አበባ በተከማቸው የቆሻሻ ጎርፍ / ናዳ የተቀበሩት ዜጎቹን አስክሬን እያወጣ በማልቀስ ላይ ይገኛል ። ይኸ ቀን በሄራዊ ሀዘናችን አድርገነዋል። እንቆጫለን። እናዝናለን ። ለቀሪ ቤተሰቦቻቸው ሀዘናችንን እናስተላልፋለን ። ሀዘናቸው ሀዘናችን ነው ። ይኸ ቁጭትና ሃዘን ፤ ትግላችንን በበለጠ አኳኋን እንድንገፋበት ይገፋፋናል ። ሀሞታችንን በበለጠ ያኮሳትረዋል ! የዚያ የየካቲት 66 ትውልድ ትግል መና ሆኖ አይቀርም። ተወደደም ተጠላ፤ ቁጭታችንን የምንዋጣብት ጊዜ መምጣቱ አይቀርም ። ጥቃትና ውርደት፤ ግፍና በደል፤ የሚፈፀምበት ሕዝብ፤ ቁጭትና ንዴት ተሸክሞ እንዲኖር አይጠበቅበትም ። ዛሬ ዳር እስከዳር የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመፅ፤ ቁጭቱን እየተወጣ ከዘረኞች የግፍ አገዛዝ የሚላቀቅበት ወቅት አብሳሪ ነው።

የሁለት ዐሃዝ ( ዳብል ድጅት ) ዕድገት አስመዝግቢያለሁ እያለ የሚመፃደቀው ይኸ በጥራኒ / ጉረኛ ቡድን፤ የአዲስ አበባን ፤ቆሻሻ ክምር ማስወገድ አቅቶት፤ የተጠራቀምው ቆሽሻ ፤ ናዳ ሆኖ፤ ለብዙ ንፁሃን ዜጎች ህይወት መጥፋት ምክንያት ሆነ ። የጀግናው ሕዝብ፤ " **ጎራዴው ሰው በላ** " የሚለው፤ አኩሪ የጦር ሜዳ ፉከራው ፤ ዛሬ **"ቆሻሻው ሰው ፈጀ "** ወደ ሚል የሀዘን እንጉርጉሮ ተለውጧል። ይኸ ሁኔታ፤ ለገመምተኛዋ ሀገር ተጨማሪ ህመም ሆኗል ። ጎመምን በመዳህኒት መፈውስ ሲገባ ፤ " ዕሾህን በሾህ" መውጣት ይመስል፤ ለህሙማን ፤ ተጨማሪ በሽታ እያመጡ ሀገርን መግደል፤የወያኔ ዓይነተኛ ተልዕኮ መሆኑን ፤ እስካሁ ድርስ ያልተረዱ ጥቂት ተስፈኞች እንዳሉ እናውቃለን ። የዛሬዋ ገመምተኛ ሀገር ስትድን ፤ የእነርሱ ጎልፈት ዕውን እንደሚሆን ፤ የሀገሩን ትንሣዔ የሚጠብቅ ዜጋ ሁሉ፤ የለመለመ ተስፋውን አንግቦ ይታገላል ። የወያኔ የበላይ ጠባቂዎች፤ ቅድሚያ የሚሰጡት ለብሄራዊ ጥቅማቸው መሆኑን ያልተከሰተላቸው የዘረኛው አገዛዝ አባሪ ተባባሪዎች ፤ ቀኑ ሳይጨለምባቸው፤ ሰልፋቸውን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ጋር ቢያደርጉ ይሻላቸዋል ። ሰው ለምን ተሳሳተ አይባልም ። ስህተቱን አርሞ የሕዝብ ወገን እንዲሆን ግን ይጠበቅበታል ። "ማረኝ -ማርኝ ፤ መባባል፤ የባጎላችን መሠረት በመሆኑ፤ ነግ- ተነገ ወዲያ የኢትዮጵያ ሕዝብ " **የምትነውም እኛ ፤ የተረፍነውም እኛ** " እንደሚባለው የአባት-አደር፤ ልምድና ባጎል፤ የተቀያየመው ፤ ይቅር -ይቅር ተባብሎ፤ እንደወተሮው በአብሮነት እንደሚኖር ማንም አይጠራጠርም ። ያን ጊዜ ነው፤ ገመምተኛው ሀገራችን፤ ከአልጋ ቁራኛ፤ ከዘረኞች መጋኛ ነፃ ልትሆን የምትችለው።

ከረዥሙ / ከስትራተጃዊው ዕይታ፤ ሀገራችን አሁን ከገጠማት ችግር ልትድን የምትችለው ፤ ምልዐተ- ሕዝቧን ያካተተ- ያሳተፈ መፍተሄ ስታገኝ ነው። እስካሁ ድረስ ይኸ አልተሞከረም ። አልተፈተነም ። በአንፃሩ ግን የሆነው ፤ **"እኛ ብቻ እናውቅልሀለን "** የሚሉ ፤ የሀገሪቱን መሠረታዊ ችግሮች ያለተረዱ ፤ ግለሰቦች የመንግሥት ሥላጣን መንጠቃቸው ነበር ። የሕዝቡን አመፅ እንደ አጋጣሚ እየተጠቀሙ ፤ ወደ ሥልጣን ጎረቻ የሚወጡ ግለ-ሰቦች የግል ምኞት ማርኪያና መፍንጫ መሆን፤ ለሀገራችን በሽታ መድሃኒት እንዳይገኝ ደንቃራ እየሆነ ቆይቷል ። ይክ ክስተት ደግሞ ፤ በሂደት ሀገሪቱን፤ ወደ ከረሰ-መቃብሯ እንድትገባ የሚያደርጋት አደገኛ ሁኔታን አስከተለ ። ችግርን የሚያባብስ- የከፋ ሁኔታን የሚጋብዝ፤ ሀገርና ሕዝብ የሚበታትን፤ ተተኪ ትውልድ እንዳይፈጠር፤ ማጎፀን- አምካኝ አጋዘዝ እንዲሰፍን ተደረገ። ሀገር ማስቆረሱ፤ ሕዝብ በዘር መከፋፈሉ እንዳልበቃ ሁሉ፤ ተተኪ ትውልድ እንዳይወጣ እየተደረገ ነው። ትውልድ መግደል፤ የወንጀሎች ወንጀል ነው ቢባል፤ ማጋነን አይደለም ። " ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባበታል ፡፡ " ደርግ አንድ ትውልድ መትሮ እንደሄደው ሁሉ፤ ወያኔዎቹም ዛሬ ትውልድ መግደሉን ቀጥለውበታል። በተለይም ደግሞ ፤ በዐማራ ወጣት ላይ የሚያደርጉት የዘር ማጥፋት ርምጃ ፤ እጅግ ሲበዛ ዘግናኝ ወንጀል ሆኗል ።

ይኽ እንዳይሆን ስጋታቸውን የገለፁ፤ አርቆ አስተዋይ ዜጎች፤ ምሁራንና መሥዋዕት- ከፋይ ትውልድ እንዲጠፉ ተደረገ። የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተስፋ ጥፍቶ፤ በናቡከደንፆር አረመኔ አገዛዝ ተተካ። የቁርጥ ቀን ቁርጠኞች እየመነመኑ ፤ የእነርሱን ቦታ ጥቅመኞች ወረሱት። ብርኅታዊ ሀገር መሆኗ እየቀረ፤ የጨለምተኝነትና የድብዝብዝ ጭጋግ ሰፈነ። ይኽ ደግሞ የሀገርና የሕዝብ መሪዎችና ጀግኖች እንዳይወጡ ዓይነተኛ ምክንያት የሆነ ነው ። ለዚህ ሁሉ ቀዳማይ ተጠያቂዎች ለአለፉት ግማሽ ምዕተ - ዓመት ( 17+ 26 የአምባገኖኖች አገዛዝ ) ሁሉት ተፈራራቂ የሥልጣን ጥመኞች ናቸው። ደርግና ወያኔ !

**1ኛ.** ከ1966 ዓም እስከ 1981 ሀገሪቱን እንዳልነበረች እንድትሆን ምክንያት የሆነው የደርግ አገዛዝ ነው። ለሐተታችን መነሻ ለሆነው ጉዳይ ግንዛቤ እንዲሆን መጠቀሱ እንጅ፤ በአሁኑ ወቅት፤ ስለ ደርግና አገዛዙ ለመተርከም ሆነ ጫና ለመስጠት ታስቦ አይደልም ። አጣዳፊና አንገብጋቢው ጉዳይም ይኽ ሆኖ አይደለም ።

**2ኛ.** እንዳንገብጋቢ ጎዳይ ሊወሰድ የሚገባው ፤ የወቅቱ ሀገራችን አሳሳቢ ችግር ነው። ለዚህ ችግር በኃላፊነት ተጥያቂው በዘር ተደራጅቶ በመምጣት ሀገሪቱን በቅኝ -ገዥዎች እቅድና ስልት ተመስርቶ በዘርና በቋንቋ ኢትዮጵያን የሚያተራምሰው አደገኛው ቡድን ነው። ሀገርንና ነዋሪዎችን በማመሰቃቀል ላይ ተጠምዶ ሀኬት ፈጠሪው ወያኔ ነው። ኢላማችን በዚህ አደገኛ የሀገርና ሕዝብ ጠላት ላይ ነው ። ከወያኔ ጋር የማይታረቅ ቅራኔ አለ ሲባልም፤ መሠረቱ በሀገራችን፤ እንደ ሀገር መኖር አለመኖር፤ ዜጎቿም በአንድ ላይ የመኖር ያለመኖር ጥያቄ ነው። ወያኔ ፤ጊዜውን እየጠበቀ የሚፈነዳ ፈንጅ እየቀበረ ሲሄድ ፤ የእኛ ተቀዳሚ ተግባር ደግሞ፤ ፈንጅው ጉዳት እንዳያደርስ እየተከታተሉ ፈንጅውን ማምከን ሆኗል ። ልዩነቱ፤ ፈንጅ በመቅበርና የሚቀበረውን ፈንጅ በማምከን ያለ፤ የሞት -ሽረት ፍጥጫ ነው።

"አገዛዙ ስለ ተወጠረ መውጫ ቀዳዳ ለማግኘት ሲል ዕርቅና ድርድር እያፈለገ ነው ። " የሚለው ከንቱ ማዘናጊያና የጊዜ መግደያ ትጥቅ አስፈች ሆኖ ቀርቷል ። "ተጨፈኑና ላሞኛችሁ " የሚለው ዘዴ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ፤ በጋርዮሽ ሥርዓት ለሚኖር ኅብረተስብ እንኳ አይሰራም ። ኢትዮጵያን የያዛት በሽታ፤ ከገፋና ከደነደነ ደርጃ የደረሰ ( አድቫንስድ ስቴጅ ላይ ያለ ) ነቀርሳ ነው ። የነቀርሳ በሽታ እዚህ ደረጃ ከደረሰ ፤ በቀድዶ - ጥገናም ( ኦፔራሲዮን ) ወይም በጨረር ( ኬሞ ቴራፒ ) የሚድን አይደለም ። የበሽተኛውን ህይውት ማትረፍ የሚቻለው ነቅርሳውን አስወግዶ በመጣል ነው ። ኢትዮጵያን ማዳን ካስፈለገ ፤ መሠረታዊው መፍተሄው/ መዳህኒቱ፤ አብነቱ ምሥጢሩ ፤ በሽታዋን ነቃቅሎ መጣል ያስፈልጋል። በመላው ዐለም የሚገኙ ተደናቂ ሐኪሞች፤ ቢሰበሰቡ፤ ሱባኤ ቢገቡ፤ ቢመክሩ፤ ቢዘክሩ፤ እየተወያዩ ቢከራከሩ ለሀገራችን መፍተሄ ሊያመጡ አይችሉም ። ከኅሎትም ብልሃትም ዕውቀቱም ሆነ ኃላፊነቱ የወደቀው በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ነው። ይኽንን ግዴታ ለመወጣት፤ ለአንዴና ለመጨረሻ የሚሆን ርምጃ እንዲወስድ ያምናል ። እርሱም ተበብሮ የጋራ ሀገሩ ጠላት የሆነውን ወያኔን በማስወገድ፤ በምትኩ ዴሞክራሲያ ሥር ዓተ- መንግሥት መመስረት ነው።

ከዚህ ድምድሜ ላይ መድረስ ከተቻለ ፤ ሀገሪቱን ወደ ተሻለ አቅጣጫ እንድታመራ በር ከፋች ዕድል ይገኛል ። በሕዝብ አመፅ በሚተከፈተው በር ፤ ለሥልጣን ያቆበቆቡ ክፍሎች ሾልከው በመግባት ፤ የዴምክርሲውን ተስፋ እንዳያጨልሙት ግን፤ ሁሉም ነቅቶ መጠበቅ አለበት ። ከእንግዲህ ወዲህ፤ ሀገርችን የአዲስ በሺታ ወረርሽኝ ሰለባ እንዳትሆን መከላከል

የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል ። በሕዝብና በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት ፤ በአውቅሁሽ-አወቅሽኝ ሳይሆን፤ በመሠረታዊ መርኅና በጋራ ስምምነት ላይ በሚገነባ ሕግ ላይ መሆን አለበት ።

እስከዛሬ ድረስ፤ ህዝቡ፤ ማር በተቀባ አሳሶች መፈክርና ፕሮፓጋንዳ ሲታለል ቆይቷል ። ብዙ አፈ-ቀላጢዎችና ሃሳዊ መስሂዎች ፤ የበግ ለምድ - ለባሽ ተኩላዎች ፤ ታግሎ ያገኛውን ድል ነጥቀውታል ። አሁንም አድፍጠው የሚጠባበቁ የሉም ማለት አይቻልም ። በማነኛውም ኅብረተሰብ፤ ውስጥ " በየአንዳንዱ 12 ሐዋርያት፤ ቢያንስ ቢያንስ አንድ አንድ ይሁዳ " እንደሚኖር፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ያውቃል ። ችግሩ ግን፤ እጅግ ጨካኝና አክራሪ ፅንፈኛ አጋዘዝ ስለሚያስመርረው ፤አዲስ የሚመጠው ሥር ዓት አራማጆች ምናልባት የተሻሉ ይሆናል በሚል ቀቢፀ- ተስፋ፤፤ " እስኪ አዲስ መጭውን እንየው ! " የሚል ጥርጣሬን ስለሚይስተናግድ ነው ። ከእንግዲህ ወዲህ፤ ይህንን ማስተናገድ የሚገባ አይመስለንም። ጉዳት ያስከትላል ።

ደርግ፤ በዐብዮት ስም ፤ ወያኔ፤ ደግሞ "በብሄር ነፃ አውጭ " ሰበብ፤ ለአለፉት ግማሽ ምዕተ- ዐመት ተዘርዝሮ የማያልቅ ግፍና በደል፤ ፈጽመዋል ። ቢሆንም፤ ዛሬ መተኮር ያለበት፤ ሀገሪቱን ከገጠማት ፍዳ በመውጣቱ ላይ ሊሆን ይገባል ። ስለአልፈው ብቻ ማዘንናም ሆነ መብተክተክ የትም ሊያደርስን አይችልም ። በተቀመጥንበት ሃዘናችን ላይ መጥቶ የሚያፅናን ማንም አስተዛዛኝ አናገኝም ። የራሳችንን የቤት ሥራ ገና አልሰራንም ። ብዙ ይቀረናል ። የቆሻሻው የበሽታ ጥንቅ ከመሆን አልፎ-ተርፎ፤ የክምሩ ናዳ የብዙሃን ዜጎቻችንን ህይወት ጨርሶታል ። የበሽታችን መክንያት፤ በዋናነት የዘረኛ በሽታ አገዛዝ መሆኑ አያከራክርም ። የዚህ ጠንቀኛ አገዛዝ ስረ-መሰረቱ ካለተመነገለ ፤ ኢትዮጵያ ጤናማ ሀገር ልትሆን አትችልም ። ጤናም ሀገርና ሕዝብ ለማግኘት ፤የበሽታውን ጥንቅ ለይቶ ፤ ነጥሎ፤ በመምታ የቅድሚያ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ።

ኢትዮጵያ ለዘለዘለም ትኖር !